ዘመቻ በማክሸፍና በመጨረሻም 3ኛ ክ/ጦርን ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ በመራኛ ካራ ምሽግና ጉጉፍቱ ላይ የተደረገው ጦርነት ነበር።

ከዚህ በኋላ 1983 የካቲት ጎጃምና ግንደርን በሙሉ ነፃ ያወጣው ዘመቻ "ቴድሮስ" ቀጥሎ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ዘመቻ "ቢሉሱማ ወልቀጡማ" ቀጥሎም ከደሴ እስከ ደብረ ብርሃን የሰፈረውን የደርግን ሰራዊት የጠራረገው ዘመቻ "ዋልልኝ" ተጠቃሶች ናቸው።

ከላይ እንደተገለፀው ዘመቻወቹ ተከታታይነት ያላቸው ለደርግ መንግስት ፋታ የማይሰጡ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ከጥቅም ውጭ ያደረጉት የደርግ ህይል በተመሳሳይ ወቅት በሻዛቢያ ከተመታው የደርግ ኃይል ይበልጥ እንደሆን እንጂ የማያንስ መሆኑ ነው።

በተጨማሪም ዘመቻወች ሰፋፊ ቀጠናዎችን ከደርግ አገዛዝ በማላቀቅ የደርግን ፖለቲካዊ መሰረት ንደዋል። የደርግን መንግስት resource (የሰው ማቴሪያል) የማግበስበስ አቅም ነስተውታል። ይህ በአጠቃላይ የጦርነቱ ሒደት ላይ የነበረው ተጽእኖ እጅግ ከባድ ነበር።

በአንፃሩ ኢህአዴግ በዘመቻ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ህዝቦች የራሳችውን አስተዳደር በመመስረት ታጥቀው ጥቅማችውን ለማስከበር ከኢህአዴግ ጋር ሆነው ለመጨረሻው ድል እንዲሰለፉ አስችሏቸዋል። ይህ ሁኔታ ለኢህአዴግ ከፍተኛ አቅም ፈጥሮለታል። በፋና ኢህአዴግ ዘመቻ ወቅት የጉና የመጨረሻው ማጥቃት ሲፈጸምና ከዛም አስቀድሞ የጋይንት፡ የዐማዳና፡ የፋረጣ ህዝበ ከኢህአዴግ ጎን ተሰልፈው ራሳቸው ያኔ የገለጹት እንደነበረው "ከኢህአዴግ ጋር ትከሻ ለትከሻ ሆነው" ባይገቡ ኖሮ ድሉን መቀዳጀት አይቻልም ነበር።

ከሁሉም ዘመቻችን የሚታይ ግልፅ ባህርይ አለ።

ከከፍተኛ ፖለቲካዊና የራስ መተማመን የሚመናጩ የዘመቻ እቅዶች ናቸው።

በከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ ላይ የተመሠረቱ ናቸዉ።

በእቅድ አወጣጥና አፈፃፀም የደርግ መንግስት ከደረሰበት ጉዳት ሳያገግም ፋታ ሳይሰጡ በላይ ላይ የሚደረቡ እናም ድምር ውጤታቸው በተናጠል ከሚያመጡት የበለጠ እንዲሆን ተደርገው የተሰሩ ናቸው።

የመንግስት ፖለቲካዊ መሠረት በመናድ የአማፂያኑን መሠረት በማጠናከር መንግስት ለቀጣዩ ሽንፈት የሚያመቻቹ ናቸው።

ይህ የዘመቻወች ቅንብር በወቅቱ በከፍተኛ ደረጃ ታስቦበት የተነደፈ ወታደራዊ እስትራቴጂ አካል ነው። ይህ አካሄድ ህወሓት ከ1977-1980 ድረስ ያደረገው ስፊ ሁሉን አቀፈ ምርምርና ጥናት ውጤት ነው። ይህንን ጉዳይ ያኔ ድርጅቱ ያወጣቸው የነበሩ ፅሑፎችን በመመርመር ማረጋገጥ ይቻላል። አሁን ግዜ ካለፈ በኋላ ተቀነባብሮ የተቀመጠ ጉዳይ አይደለም።

ፀሐፊው ይህንን ጉዳይ በተገቢው መንገድ የመረመሩ አልመሰለኝም። ይህ በመሆኑም የሽሬ ውጊያ ሲፅፉ ለፀሐፊው ሳይቀር ድንገት ነው የሆነባቸው (ገጽ 262)። በእኔ ግምት በውጊያወቹ ላይ ያለው ትንተና ከአንድ በስፋት የሚሰራጭና በስፋት በመሰራጨቱ ደግሞ ተቀባይነት እያገኘ ከሄደ አስተሳሰብ በመነሳት ይህንኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል  የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ እየተካሄደ አስመስሎታል። ይህ በ መሆኑም የህወሐት/ ኢህአዴግ ወታደራዊ ፈልሚያወችና ድሎች ዋናውን የሻእቢያን ጥረት ለማጀብ የተካሄደ አስመስለዋቸዋል። ይህ አስተሳሰብ በእኔ እምነት ሻዛቢያ ከሚያምንበት በትጥቅ ትግሉ ወቅት የደርግን መንግስት ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ታሪክን ያላገናዘበ አሸንፌለሁ ወደሚለው አስተሳሰብ የቀረበ ነው። ይህ ደግሞ የአካባቢያችንን ሰላም የሚያውክ አስተሳሰብ ነው።

## 4. ሌሎች

ፀሐፊው በመጽሃፋቸው ያነሱዋቸውን ሁሉንም ዝርዝር ጉዳዮች ማንሳት አያስችልም። ለእኔም ተለቅ ተለቅ ያሉ የመሰሉኝ አነሳለሁ።

የህወሐት ሰራዊት ከቀይ  ኮከብ  ዘመቻ መጀመር ጥቂት ቀደም ብሎ (በዘመቻው ለመሳተፍ) እስከ 1977 ዓ/ም አጋማሽ ድረስ ሦሥት ብርጌዶች (እንድ የህወሐት ብርጌድ ያኔ ከ1200-1500 ድረስ የሰው ሃይል ነበረው) እዛው ተሰልፈው ሻህቢያን ደግፈዋል። ኋላ ኋላ የሚወራው ወሬ የተለየ ሆነ እንጂ በወቅቱ ሲነገር የነበረው ጉዳይ  ኋላ ከሚነገረው የተለየ ነበር።

ሻህቢያ ህወሐትን በኋላም ኢህአዴግን የደገፈው በሽሬ ውጊያ የመጨረሻው ምዕራፍ ለይ ነበር። ይህም የደርግ አራተኛ ክ/ጦር አራት ታንኮችን ካቃጠለባቸው በኋላ ሸሽተው ወደ ኋላ ተመልሠዋል።ሻህቢያ ይፈጽመዋል ተብሎ ታስቦ የነበረው ግዳጅ በህወሀት ክ/ጦሮች (አውሮራ እና አሉላ) ፈጽመውታል። ሌላው ሻህቢያ የተሳተፈባቸው ውጊያወች  በ1983 የካቲት በተጀመረው ዘመቻ ቴድሮስ ጀምረው እስከ እዲስ አበባ ገብተዋል።  በዙህ የ 4 ውራት (ከየካቲት እስከ ግንቦት-) የቆይታ ግዜችው በጠቅላላ ከ 300 እስከ 350 የሚደርሱ የሻእቢያ ወታደሮች ከ 85 ሺ.ህ በላይ

ቁጥር ከነበረው የኢሃዴግ ሠራዊት ጋር ተቀላቅለው ተዋግተዋል፡፡ ጦርነቱ እንዳለቀ በግምት ከሁለት ሳምንት የአዲስ አበባ ቆይታ በኋላ በ10 የአንበሳ አውቶብሶች አሳፍረን ወደ ስመራ መልሰናቸዋል፡፡

እንግዲህ በሦስት ብርጌዶች እነዚህም ብርጌዶች ይመሩና ያስተባብሩ ከነበሩት ከፍተኛ አዛዦች ጋር በተከታታይነት ለሦስት አመት የዘለቀው የህወሓት ድጋፍ እንደ ፉት ኖት ሆኖ ሲፃፍ ለአራት ወራት በ300 ወታደሮች የተደረገው ተሳትፎ የታሪኩ ዋና አካል ሆኗል፡፡ ይህ ነባራዊ ሁኔታውን አይገልፅም፡፡

ፀሐፊው በህወሐት እና በሻህቢያ የነበረ የሚሉትን መመሳሰል ሲገለፁ የመመሳሰሉ ምክኒያት ሻህቢያ ህወሐትን ስላሰለጠነው እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በእርግጥ የተወሰኑ የህወሀት መሪወች ሻእቢያ አሰልጥኗል ፡፡ ያሰለጠነው ስለወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ ስለወታደራዊ እስትራቴጂ እና ታክቲክ አይደለም፡፡ ያሠለጠነው መውደቅ መነሳት ነው፡፡ መተኮስ እንኳን በወጉ አላሰለጠናቸውም፡፡ ከነአንካቴው መውደቅ መነሳቱንም ያሰለጠነን የህወሀት ወታደራዊ መሪዎች እጅግ በጣም ብዙወቻችን ነን፡፡ የሻእቢያንና በኢህአዴግ ወታደራዊ እስትራቴጂ የተለያየ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዛ የተማርነው ወታደራዊ አስተሳሰብና ችሎታ አልነበረም፡፡

በመጽሐፍ ላይ ገፅ 298 ላይ ስለጉና ተራራ ውጊያ የሚያወራውና የሦሥተኛ ክ/ጦርን በተመለከተ የተቀመጡት ሁለቱም መረጃዎች የተሳሳቱ ናቸው፡፡ ጉና ተራራ ላይ ውጊያ የተደረገው የዘመቻ ፋና ኢህአዴግ አካል ተደርጎ ነው፡፡ ይህም የካቲት 1982 ነው፡፡ በመፅሐፉ የተገለፁ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ችግሮች አጋጥመው ነበር፡፡ ግን ከወራት በኋላ ተፈትተው ደርግ ለጊዜውም ቢሆን ባህር ዳርን ሳይቀር ለቆ እንዲወጣ ያስገደደውን የ603 ኮር ኃይልን በመደምሰስ የተገባደደ ዘመቻ ነበር፡፡ አንድ ዓመት ሙሉ ችግሩን በመፍታት ላይ ተቀምጠው ነበር የሚለው ትክክል አይደለም፡፡ ከ1980 ዓ/ም በኋላ ትልቅ ዘመቻ ሳይካሄድ ለአንደ ዓመት የተቀመጥንበት ወቅት አልነበረም፡፡ በአማካይ በየ 6 ወሩ ትላልቅ ዘመቻወችና እነሱን የሚያጅቡ ውጊያዎች እናካሄድ ነበር፡፡

ሦስተኛ ክ/ጦር ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በመጨረሻ ግዜ ከጥቅም ውጭ የሆነው ከ 1982 ክረምት ላይ በተደረገው የመራኛና ኮራ ምሽግ ውጊያ ነው፡፡ ወደ አዲስ አበባ ስንገባ አልነበረም፡፡ ለነገሩ ከዚህ ክ/ጦር ጋር ብዙ ግዜ ተዋግተናል፡፡

ፀሐፊው በቅርቡ ስለተደረገው የኢተዮጵያና የኤርትራ ጦርነት ጥቂት ብለዋል፡፡ በእኔ ግምት ይህ አላስፈላጊ ነበር እላለሁ፡፡ ሆኖም የተቀመጡ የተሳሳቱ

መረጃዎች አሉ፡፡ በዚህ ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ጉዳት እጥፍ ነበር ብለዋል፡፡ ይህ ጋዜጦች ከሻህቢያ አፈ ቀላጤ በመውሰድ ያስቀመጡት ቁጥር ነው፡፡እንደ ታሪካዊ መረጃ መቀመጥ አይገባውም፡፡ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ የኢተዮጵያ ሰራዊት የኤርትራን ሰራዊት እጥፍ ጉዳት ደርሶበት አያውቅም፡፡

በመጨረሻም በመፅሐፍ ውስጥ አልፎ አልፎ በታሪካዊ ሂደቱ ውስጥ ከፍተኛ ተራ ነበራቸው ብለው ፀሐፊው የሚያምኑባቸውን ግለሰቦች በመጥቀስ ያላቸውን ሚዛን አስቀምጠዋል፡፡ ከዙህም አልፈው በፖለቲካዊ ድርጅቶች ላይ ሚዛናዊ አስተያየት አስፍረዋል፡፡ በተለይም ከኢህአፓ ተነጥለው መጀመሪያ ኦህዴን በኋላም ብአዴን በመሠረቱትና በመሩት ሰዎች ላይ የተቀመጠው ሚዛን ፈሩን የሣተ ይመስለኛል፡፡ በፖለቲካዊ መስመሩ አለመስማማት ካለ ይህንን ሀሳብ መግለፅ ትክክል ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ትግል ማካሄድ ተራራን በገመድ የመጎተት ያህል የማይቻል ነው እየተባለ፤ ሰው ወደ ለንደንና አሜሪካ በሚፈረጥጥበት ወቅት፤ እስኪ የፖለቲካ መስመሩን ሌላ አቅጣጫ አስግዘን እንታገል ባሉት ላይ ከዳተኞች የሚል የፖለቲካ ስድብ ማስቀመጥ ተገቢ አይደለም፡፡(ገፅ______)

በማጠቃለል ስራው ገና እየተጀመረ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀኝ ስራውን መጀመራቸው ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ጉዳዩ ግን በላይ በላዩ ከሚታየው አልፎ ጠለቅ ያለ ጥናትና ለወደፊቱ ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን መቅሰም በምንችልበት መንገድ ማስኬድ ይጠይቃል፡፡

አመሰግናለሁ

ሌ/ጀነራል ገ/ፃድቃን ገ/ትንሳኤ

የ ኢ.ፌ.ድ.ሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም

(1983-1993)